# ቢብስ እንጂ ፡ አያንስም

ወፍ እንደሚበላው ፣ ቀድሞ ያሸተውን
ሰውም ይጠላዋል ፣ ቀድሞ የተቸውን
ያፋሽና አጎንባሽ ፣ ትችቱ ተፈርቶ
ቤትክን ሲያፈራርስ ፣ ከማጀትህ ገብቶ
አንድም አድር ባይ ነህ ፣ አሊያም ቦቅቧቃ
ሌባ ቤቱን ሲዘርፍ ፣ አውቆ የማይነቃ ።

ከመረቁ አውጡልኝ ፣ ከስጋው ያመኛ
እንዲ ያለ ጨዋታ ፣ አይገባንም እኛ
ይብጠለጠላሉ ፣ እስኪቅለሸለሹ
ይሄ ካልጣማቸው ፣ ከስልጣን ይሸሹ
የስልጣኑን ግርፊት ፣ ወላፈን የፈራ
ሰብሰብ ማለት ነው ፣ ከዙፋኑ ተራ
አብይ ሆነ ለማ ፣ አይደሉም ስላሴ
ለነሱ የሚቀርበው ፣ ዘወትር ውዳሴ
ወንበሩ ተወዶ ፣ ትችቱ ተጠልቶ
እሱ አይታሰብም ፣ ዋልድባም ተገብቶ ።

ሙሴ የተባለው ፣ አለልክ ተክቦ
ቋንቋ ጎሳ ሳይለይ ፣ በሁሉ ታጅቦ
አላማው ሲሳካ ፣ ከዙፋኑ ቀርቦ
እግሩ ሲደላደል ፣ በቢጤው ተከቦ
ከመርፌ ቀዳዳ ፣ አስር ጊዜ ጠቦ
በኦነግ ሰራዊት ፣ አዲሳባን ከቦ
ዜጋን ሊያፈናቅል ፣ ሊያጋይ እንደችቦ
አሰፍስፎልሃል ፣ አፍንጫህ ስር ቀርቦ
ሊጠራርግህ ነው፣ልክ እንድ ተስቦ ።

በግርግር መስከር ፣ ትግላችን አይጠራ
ማንነት አንጠይቅ ፣ ለመጣው ጭፈራ
ሲፈራረቅብን ፣ የማንም መንጃራ
ከማወደስ በቀር ፣ መተቸት ስንፈራ
ሁሌ እንዳለቀስን ፣ ወጥተን ከሰው ተራ
የት ይደርሳል ማለት ፣ ዘወትር ፉከራ
በለማና በአብይ ፣ የታቀደው ሴራ
እንጎቻ እንዳይመስልህ ፣ የናትህ እንጀራ
ቢብስ እንጂ አያንስም ፣ ካለፈው መከራ ።

ታዛቢው

March 3, 2019